# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ደቡብ አፍሪካ ለህብረቱ ሊቀመንበር እጩ በማቅረብዋ አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች ተደናገጡ፤፤**

**በአፋር አሁንም ችግር መኖሩ ተጠቆመ፤**

**ጥምቀት በዓል ደምቆ ተከበረ-ወጣቱ ብሶቱን ሲያስተጋባ ተደመጠ፤**

አምባገነን የአፍካ ሀገራት መሪዎች የተሰባሰቡበት 18ኛው የመሪዎች ስብሰባ በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገበት ወቅት ህዝቡ መላወሻ መተንፈሻ አጥቶ ከመክረሙም በላይ በደህንነት ግልምጫና ቁጣ እየተንገላታ እንደሰነበተ ታወቀ::

ከጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ተከታታይ ቀናት በተካሄደበት በዚሁ የመሪዎች ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ የተገኙ ቢሆንም በስበሰባው ላይ ለህዝባቸውና ለሀገራቸው ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ፋንታ በተድበሰበሰና እከከኝ ልከክልህ በሆነ ስሜት ውይይት ሲያንሂዱ መሰንበታቸው ታውቆዋል::

ከመቼውም ግዜ በላይ ዘንድሮ የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ ለየት ያለና ብዙ ንትርክ ሲያደርግበት የተስተዋለው ለህብረቱ ሊቀመንበርነት ደቡብ አፍሪካ ተመራጭ በማቅረብዋ አምባገነን መሪዎች እጅግ የደነገጡበት እና ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበረበት መሆኑ ነው::

እስከ ዛሬ ድረስ ከአነስተኛ ሀገሮች የሚመረጡትን እነ መለስ እንዳሻቸው በጥቅም እየገዙ ሲያሽከረክሩዋቸው የነበሩትን ግለሰቦች እየሾሙ ሲያስቀምጡ የነበረ ሲሆን ዘንድሮ ግን ለህብረቱ ሊቀመንበርነት የደቡብ አፍሪካው የሀገር አስተዳደር ሚኒስትርዋ ዲላሚና ዙማ በመቅረባቸው ያልተጠበቀ ድንጋጤ በአምባገነን መሪዎቹ ዘንድ መፈጠሩም ታውቆዋል::

ከአሁኑ ሊቀመንበር በፊት የነበሩት እነ ብሌስ ኮምፓወሬም ሆኑ የአሁኑ ጃን ፒንግ ለአፍሪካ ህዝቦች አንዳችም ፋይዳ ያልፈጸሙ ይልቁንም የእነ መለስ ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነው ሲያገለግሉ ከመቆየታቸውም በላይ የህዝቦችን መብት ሲጨፈልቁና ሲያስጨፈልቁ የነበሩ መሆናቸውን ያስታወሰው

ዘገባ የአሁንዋ የደቡብ አፍሪካ እጩ ተፎካካሪ ከተመረጡ ግን ሁኔታዎች ለአምባገነን መሪዎች አስደንጋጭ እና እጅግ አሳሳቢ እንደሆነባቸውም ከህብረቱ ፅህፈት ቤት የሚወጡ ጥቆማዎች ያስረዳሉ።

ግለሰብዋ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ በተደረገው የሙስና ማጽዳት ዘመቻ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ከመሆኑም በላይ ያመኑበትን የሚያራምዱ እጃቸውን ተይዘው የማይጠመዘዙ በመሆናቸው ለነመለስ ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነባቸውም ተጠቁሞዋል።

የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት እጩዋን ሲያቀርቡ ባደረጉት ንግግር አፍሪካ በዓለም ፊት ጠንካራ ተፎካካሪ ሆና ለመቅረብ የማስፈጸም አቅም ያላቸውን ግለሰብ ማወዳደር ግድ ስለሚል እጩዋን ለማቅረብ እንደተገደዱ ገልፀው በተለይ በአፍሪካ ውስጥ ዲሞክራሲን ለመገንባት ለሚደረገው ትግል ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ ብለን ስላመንባቸው ነው በማለት ገልፀዋል።

ደላሚና ዙማ በደቡብ አፍሪካ በተደረገው የዲሞክራሲ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ከመሆኑም በላይ ሙስናን ለማጥፋት ከዘመቱ ሚኒስትሮች ግንባር ቀደም ተጠቃሽ መሆናቸውን የጠቀሰው የህይወት ታሪካቸው አሁንም በህብረቱ ውስጥ የሚፈጸሙ ዝርክርክ አሰራሮችን አጽድተው አንድ እርምጃ ወደፊት ሊያስኬዱ ይችላሉ ተብሎ ስለታመነበት ወደ ምርጫው እንዲገቡ መደረጉን ደቡብ አፍሪካ ገልጻለች።

በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተደረገውን ሀገር አቀፍ ምርጫ የወያኔ ቡድን ሙሉ ለሙሉ በዝረራ የተሸነፈበት ቢሆንም የወቅቱ የህብረቱ ሊቀመንበር ከእነ መለስ ዜናዊ የእጅ መንሻ ተቀብለው ውጤቱን የተገላቢጦሽ አድርገው ለዓለም መገናኛ ብዙሀን መግለጫ ሲሰጡ የነበረ መሆኑን ያስታወሰው ዘገባ አሁን የደቡብ አፍሪካዋ ተመራጭ ቦታውን ከተረከቡ አምባገነን መሪዎች እና በሀሰተኛ ማጭበርበር ስልጣን ላይ የተቀመጡ መሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ሊገጥማቸው እንደሚችል በመስጋት ከወዲሁ ከፍተኛ የተቃውሞ ዘመቻ ጀመራቸው ታውቆዋል።

ስብሰባው በተደረገበት ወቅት የወያኔው ቡድን በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ እንደተደረገው ሁሉ በዚህም የህዝቡ ቁጣ ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ፍርሀት እና ስጋት እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ምልመል የደህንነት ወጣቶችን ከትግራይ አምጥቶ መላ ሀገሪቱዋን ከማዳረሱም በላይ በህዝብ ቁጥር ልክ ያህል እንዲቀላቀሉ አድርጎዋል።

ለ20 ዓመታት በአራት ኪሎ ቤተመንግስት ውስጥ የተጎለተው የህወሀቱ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ከዚህ በሁዋላም ለሌላ 40 ዓመት ለመዝለቅ እድሜዬን የማቱ ሳላ ያድርግልኝ ብሎ እጅግ በሚያሳፍር እና በሚያስቅቅ ሁኔታ በሀገር እና በህዝብ ላይ ግፎችን እየፈጸመ ከመሆኑም ባሻገር ህዝቡ እንዳይናገርና እንዳይላወስ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ደህንነቶችን በመሀል አዲስ አበባ በትኖ መላወሻ አሳጥቶት የሚገኝበት ወቅት ላይ መድረሱም ታውቆዋል።

የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች አዲስ አበባ ለስብሰባ ይገባሉ ተብሎ ከተነገረበት ግዜ አስቀድሞ በከተማዋ እጅግ ከፍተኛ ውጥረት ከመንገሱም በላይ ህዝቡ ለወትሮው የትራንስፖርት አገልግሎት

ከሚያገኝበት ቦታ በብዙ ኪሎ ሜትሮች በእግሩ እንዲሄድ ከመደረጉም በተጨማሪ ወደ ግራና ቀኝ እየዞረ እንዳይመለከት ጭምር ወከባና እንግልት ሲደርስበት ነው ሳምንቱን ያሳለፈው።

በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ አንዳንድ የአዲስ አበባ መንገዶች ለትራፊክ አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ተዘግቶ በመሰንበቱ ህዝቡ መንቀሳቀሻ ከማጣቱም በተጨማሪ ሰርቶ በሌው ደሀ ህዝብ የእለት ጉርሱን ጭምር እንዳያገኝ ተደርጎ የታፈነበት ሳምንት ነበር።

የአፍሪካን ሀገራት በሰላማዊ ቀኝ አገዛዝ ስር እየከተተች ያለችው ቻይናም ቢሆን በስውር የስለላ ካሜራ ግድግዳው በሙሉ የተገጠመለትን የአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ገንብታ ማስመረቋ ታውመቂ።

መለስ ዜናዊን የመሳሰሉ አምባገነን መሪዎች የታጨቁበት ይሄው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ዛሬ በመላው አፍሪካ ውስጥ ድህነት ተንሰራፍቶ..... ሙስና ተስፋፍቶ.....የስልጣን ጥመኝነት ከመቼውም ግዜ በላይ ፋፍቶ ባለበት ወቅት ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳይወያዩ ይባስ ብሎ እርስ በርስ ሲሞከሻሹበት ነበር ያሳለፉት።

አምና ልክ በዚህ ወቅት አምባገነኑ የቱኒዚያ መሪ በህዝብ ተቃውሞ በርግጎ ሀገር ጥሎ ከወጣ በሁዋላ ......እራሱን ከአምላክ ጋር እያወዳደረ የነበረው የሊቢያው መሪ ሙአመር ጋዳፊ በዚህ ስብሰባ ላይ ይገኛል ተብሎ ቢጠበቅም በፍርሀት ሳይመጣ የቀረ ሲሆን የግብፁ መሪ ሆስኒ ሙባረክም በአጣብቂኝ ውስጥ ሆኖ የነበረበት ወቅት እንደነበር ያስታወሰው ዘገባ እነሆ ዛሬ ላይ ሆነን አንዱን አምባገነን በሞት...... አንዱን በስደት...... ሌላውን በእስር ላይ...... አድርጎ ያለፈው ዓመት የተጠናቀቀ ቢሆንም ዛሬም እነሱን መሳይ ዘግናኝ ግፍ በህዝቦቻቸው ላይ የሚፈጽሙ መሪዎች በታጨቁበትና አምባገነኖች በነገሱበት የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ መካሄዱ ትርጉም የሌለው መሆኑንም ምሁራኖች እየተቹ ይገኛሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአፋር ክልል ልዩ ስሙ ኤርታኢሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ባለፈው ሳምንት ሰኞ ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም በታጣቂዎች በተሰነዘረ ድንገተኛ ጥቃት አምስት የውጭ ሀገር ዜጎች ሲገደሉ ሌሎች አምስት ደግሞ ተጠልፈው መወሰዳቸው ታወቀ።

ሀገር ሰላም ነው እያለ የወያኔ ቡድን ባዶ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ባለበት...... ከህዝብ ይሁንታ ውጭ በሱማሊያ ውስጥ ገብቶ እየዳከረና ከፍተኛ ኪሳራ እየተከናነበ ባለበት በዚህ ወቅት በአፋር ክልል ኤርታኢሌ በሚባለው አካባቢ ለጉብኝት በተጉዋዙ የውጭ ሀገር ዜጎች ላይ የሞት፤የመቁሰልና የመታፈን አደጋ መድረሱ ሀገሪቱ ውስጥ ውስጡን ሰላም እጦት እንዳለባት የሚያመላክት ነው ሲሉ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የተለያዩ ሀገራት አማባሳደሮች ገለፁ።

ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን አስጎብኚዎች እየተመሩ ወደ ክልሉ ሌሊት በመጉዋዝ ላይ እንዳሉ ድንገት በታጣቂዎች ተኩስ ተከፍቶ ሁለት የጀርመን፤ ሁለት የሀንጋሪ እና አንድ የኦስትሪያ ዜግነት ያላቸው ቱሪስቶች ሲገደሉ ሌሎች የጀርመን እነማ የኢትዮጵያ ዜጎች ደግሞ ታፍነው የደረሱበት ያልታወቀ መሆኑ ተገልፆዋል።

አፈናና ግድያው በተከናወነ ዕለት ጀምሮ የውጭ ሀገር ሚዲያዎች ሲዘግቡ የነበረ ቢሆንም ወያኔ ግን በሀገሪቱ ሰላም ሰፍኖዋል እያለ ምንም እንዳልተፈጠረ ሲለፍፍ ከመቆየቱም በላይ ድርጊቱ ከተፈፀመ አምስተኛው ቀን በሁዋላ አምኖ ይፋ ማድረጉ ያስቆጣቸው የሙዋች ሀገራት አምባሳደሮች ግድያው በአስቸኩዋይ እንዲጣራ ሲሉም መመሪያና ማስጠንቀቂያ ለወያኔ መስጠታቸው ታውቆዋል፡፡

ምንም እንኩዋን የወያኔ ቡድን ድርጊቱን የፈጸመው የሻእቢያ ቡድን ነው በማለት መግለጫ ቢሰጥም እራሱን የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ብሎ የሚጠራው ቡድን ግን ጥቃቱን የሰነዘርኩት እኔ ነኝ በማለት የወያኔን ግምት ያጣጣለ መግለጫ ማውጣቱ ታውቆዋል፡፡

አርዱፍ የተሰኘው ይሄው የወያኔ ተፋላሚ ቡድን ባወጣው መግለጫ በስፍራው እና በእለቱ የተሰነዘረውን ጥቃት እንደወሰደና ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ጨምሮ አስታውቆ ድርጊቱ የተፈጸመው ከወያኔ ጦር ጋር በገጠመው ውጊያ መሆኑንም በመግለጫው ላይ ይፋ አድርጎዋል፡፡

ከ20 ዓመት በላይ በቦታው በትጥቅ ትግል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የጠቀሰው ይሄው የአርዱፍ መግለጫ በአካባቢው ማንኛውም የታጠቀ ኃይል እንዳይገባና እንዳይንቀሳቀስ ማስጠንቀቂያ ብሰጥም እብሪተኛው የወያኔ ቡድን ግን በማን አለብኝምነት ሰርጎ እየገባ በመሆኑ ግጭቱ ሊከሰትና አደጋውም ሊፈጠር እንደቻለ በመግለጫው ገልጾዋል፡፡

ወያኔ በበኩሉ ድርጊቱን የፈጸሙት ሻእቢያ እና የሻዕቢያ ተላላኪ የሆኑት ናቸው ካለ በሁዋላ ከእንግዲህ እጄን አጣጥፌ አልቀመጥም.....አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ ሁሉ እወስዳለሁ ...... ሲል የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ መሆኑን በይፋ ገልፆዋል፡፡

የህዝብ ድጋፍ የሌለው ይሄው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን ምንም እንኩዋን በሻዕቢያ ላይ የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ቢሆንም በውስጥ ችግሮቹ የተተበተበ በመሆኑ እያቅራራና እያስፈራራ እንዳለው ወደ ጦርነት የማይገባ ነው ያሉት የፖለቲካ ተንታኞች በተለይ  በህዝቡ ላይ በሚያደርሰው ጫና እና የግፍ አገዛዝ የተነሳ አምርሮ በመቃወሙ  ስጋት ውስጥ መግባቱም ይታወቃል ብለዋል፡፡

ሰሞኑን በአፋር ክልል በተከሰተው የግድያና የአፈና ተግባር ላይ የተሳተፈው የሻዕቢያ ቡድን ነው እያለ ከመለፈፉም ባሻገር አይቀጡ ቅጣት እቀጣዋለሁ እያለ ቢፎክርም ወያኔም ውስጡን እርስ በርስ በመጠላለፍ እና በመነታረኩ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ያለ በመሆኑ እንዳሰበው ወደ ጦርነት እንደማይገባም እነዚሁ የፖለቲካ ተንታኞች ይገልጻሉ፡፡

በተለይ ይላሉ እነዚሁ ተንታኞች ወያኔ አዳዲስ ቀፍዳጅ እና አሳሪ ህጎችን እያወጣ ህዝቡን አላላውስ ከማለቱም ባሻገር ህዝቡ ሰርቶ እንዳይገባ በደህንነት እና በፌዴራል ፖሊስ የአፈና ተግባር እየፈጸመበት በመሆኑ ህዝቡ ከመቸውም ግዜ በላይ ጥላቻውን በገሀድ እየገለጸ በሚገኝበት በዚህ ግዜ የህዝብ ድጋፍ አገኛለሁ ብሎ ወደ ጦርነት ከቶ ሊገባ አይችልም ሲሉም አጽንኦት ሰጥተው ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

አክለውም ሰሞኑን በራዲዮና ቲሌቪዥን ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ሲያሰራጭ የከረመው የወያኔ ቡድን ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ሻዕቢያን አወገዘ በሚል የተሰራው ድራማ አሳፋሪና ለማስመሰል ከመሆን የዘለለ

አይደለም ያሉት እነዚሁ ወገኖች በሀገሪቱ አንዳችም የታጠቀ ተቃዋሚ የለም ለማሰኘት ጭምር የፈጠረው መሆኑን ዲፕሎማቶች ጭምር ጠንቅቀው አውቀውታል ሲሉም ይተቻሉ።

በአፋር ክልል በሰመራ እና አሳይታ ከተሞች ህዝቡ ለልማት ስራ ተብሎ በተጠራበት ወቅት ባንዲራና የተፃፉ መፈክሮችን አስይዞ ወያኔን ደግፎ አርዱፍን አውግዞ የዋለ ለማስመሰል የተሞከረ ቢሆንም መላው የሀገሪቱ ህዝቦችና ዲፕሎማቶች የተሰራውን ድራማ ጠንቅቀው በማወቃቸው ወያኔ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ እንደደረሰበትም ጨምረው ገልፀዋል።

አርዱፍ የተሰኘው ከወያኔ ጋር የሚፋለመው ታጣቂ ኃይል ቅዳሜ ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም ይፋ ባደረገው በዚሁ መግለጫው ላይ እንዳለው ከሆነ የታገቱት ሰዎች በጥሩ ሁኔታ የሚገኙ ሲሆን እነሱን ለማስፈታት የሀገር ሽማግሌዎች የጀመሩ በመሆኑ የወያኔ ቡድን ጣልቃ እንዳይገባም ጭምር ማሳሰቡ ታውቆዋል።

ተጠልፈው የተወሰዱትን ሁለት ኢትዮጵያዊና ሁለት የውጭ ሀገር ዜጎች ለማስለቀቅ ሽምግልና የተጀመረ ሲሆን እርምጃውን ወስጃለሁ ያለው አርዱፍ ከአፋር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን የወያኔን ቡድን እንደሚታገሉ ቃል እንዳስገባቸውም ከስፍራው የወጡ ዜናዎች ጠቁመዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ከእንግዲህ ወዲያ ወያኔ የሚሉት አውሬ ወደዚህ ክልል እንዳይገባም መላው የአፋር ዜጋ ትግል ማድረግ እንዳለበትም በምስጢራዊ ስምምነቱ ላይ እንደሰፈረም ተጠቁሞዋል።

አምስቱ የውጭ ሀገር ዜጎች ከመገደላቸው በፊት 25 የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ታግተው ማስጠንቀቂያ ተሰጥ ተዋቸው የነበረ መሆኑ ታውመቁ።

በተያያዘ ዜና ዜጎቻቸው የሞቱባቸውና የታፈኑባቸው የጀርመን ፤የሀንጋሪ እና የኦስትሪያ ሀገራት በዜጎቻቸው ላይ ስለተፈጸመው ግድያና አፈና ዝርዝር መግለጫ በአስቸኳዋይ ወያኔ እንዲያቀርብላቸው ጠየቁ።

ሀገራቱ ሰሞኑን በአምባሳደሮቻቸው በኩል በሰጡት ማስጠንቀቂያ መሰረት በአፋር ክልል ኤርታሌ አካባቢ በተፈጸመው አፈናና ግድያ ዙሪያ ገለልተኛ አካል እቦታው ድረስ ሄዶ አረጋግጦ መግለጫ እንዲሰጠን ሲሉ ከረር እና መረር ያለ ትዕዛዝ ለወያኔ መስጠታቸው ታውቆዋል።

በመጨረሻም ዘንድሮ በተደረገው የጥምቀት በዓል ላይ ህጻናት እና ወጣቶች የእለት ጉሰርስ ማግኛ ብለው ማስቲካ.....ከረሜላ.....ብስኩት እና ሶፍት በመሸጥ ላይ እንዳሉ በወያኔ ደህንነቶች መከልከላቸውና ንብረቶቻቸውም እንደተቀሙ ከአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ።

በህዝቡ መሀከል እየዞሩ በመሸጥ ትርፍ ከሚያገኙት ሳንቲም እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ሲሩዋሩዋጡ የነበሩትን ህጻናት የወያኔ የደህንነት እና የፌዴራል ፖሊሶች ከማባረራቸውም ሌላ ቀረጥ ክፈሉ ብለው በግዳጅ 50 ብር እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ ሲደረግ የተቀሩት መክፈል የማይችሉት ንብረቶቻቸው ተወርሶ በየቀበሌው አስተዳደር እንደተወሰደባቸው ታውቆዋል።

በዘንድሮ የጥምቀት በዓል ችግር ይፈጠራል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ወጣቱ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ታቦታቱን ከብቦ እየጨፈረ በማመስገን የተዋጣለት በዓል እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ በህብረት በመሆን መለስን ሲያወግዙ ተደምጠዋል፡፡

የፌዴራል ፖሊሶችንና ደህንነቶቹን ሲመለከቱ አንመካም በጉልበታችን እግዜአብሔር ነው የእኛ ሃይላችን.......እያሉ በያሬዳዊ ዜማ ሲቀባበሉ የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ መለስ ሀገሪቱን ለድህነት ህዝቡዋን ለባርነት ዳርጉዋታል ሲሉም መደመጣቸውን ከተለያዩ ቦታዎች የደረሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ፡፡

ፌዴራል ፖሊስም የወጣቶቹን መዝሙርና መፈክር ቢሰማም ችግሩ የከፋ ሊሆን ይችላል በሚል አንዳችም እርምጃ ካለመውሰዱም ሌላ አንዳንድ የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ወታደራዊ ዩኒፎርማቸውን ለብሰው ከወጣቶቹ ጋር ተቀላቅለው መለስንና ቡድኑን ሲያወግዙ እንደነበረም ከአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡